# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 2 ልዩ ዕትም 1 መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ ሺህ ፯ ዓ.ም.

## <u>ብዙ ነገር አውርሶ ያለፈ፦ ዶር ተስፋዬ ደበሳይ</u>

*(መጋቢት 15 ቀን 1969 ዓ.ም. ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ የተሰዋበትን 38ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*

<u>**ደም!**</u>

...


**ደም!** ዳቦ ለተራበው እያለ የነጎደ
በዓመጽ ውስጥ የተረጨ
የመራራውን ትግል ሂደት የቋጨ
ከዋዜማው ጋር የተጫጨ

**ደም!** የትግል ጥሪ ደወል ደዋይ
ለተከታዩ ወኔን አዳይ
...

**ደም!** አልገዛም እያለ ሚስገመገም
አልጨቆንም እያለ ሚተም
ለአርነቱ አብሮ ሚያድም

**ደም!** የዚያ የጭቁን
የታረደ በሽፍንፍን

**ደም!** የዚያ የጨቅላ
የታረደ በሰው በላ



ዶር.ተስፋዬ ደበሳይ
Dr. Tesfaye Debessay
የኢሕአፓ አመራር አባል (EPRP Leadership member)

**ደም** ቢሉ የአህያ ደም እንዳይመስልህ
**ደም** ቢሉ የውሻ ደም እንዳይመስልህ
ቀን ይዞልህ ያረከስከው ከሽንትህ
...

የ**ደም** ጐርፍ
በየአስፋልቱ በየቦዩ ተንቆርቁሮ
ያውም የሎጋዬ የጉድሮ
አውአፍ ተንጫጨ
በታጋይ መታረድ ተቆጨ
...

ፍረጂን ምድሪቷ
በታጋይ **ደም** የተዋብሽቷ
ፍረጂን ጉውዟ
የታጋይ **ደም** እርጉዟ
ፍረጂን ሰንደቂቷ በታጋይ **ደም** የቀለምሽቷ
ፍረጂን ማጭድ መዶሻዬ
የድል ጎህ ቀዳጅ አርማዬ
ፍረጂን ቀይ ኮከብ መሪዬ
የጨለማ ጉዞ ብርሃን አዳዬ

**ደም! ደም! ደም!**

APR 1 9 1977

« . . . የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ፍላጐትና ትግል ፣ በአብዮታችን ጉዳና ገፍተው ብሔራዊ ነፃነቷ የተከበረ ፣ አዲሲት ሕዝባዊትና ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያ እንድትገነባ ነው. . . »

# አዲስ ዘመን

« . . . የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች፣አብዮታቸውን ለመንከባከብና የአብዮታዊት እናት አገራቸውን ክብርና ወሰን ላለማስደፈር ፣ በተመሰከረበት ጀግንነታቸው እንደአንድ ሰው ተነሥተው በጠላቶቻቸው መቃብር ላይ ሳይቆሙ በፊት የመዘዙትን የአብዮት ሰይፍ ከእፎቱ አይመልሱትም ። . . . »

ስልክ 112041 — 111035 — 114953 — 110903 117441—120795—111692—118742—118602

« ኢትዮጵያ ትቅደም »

የማስታወቂያ ክፍል .......... 119050-119837
የሂሳብ ክፍል .................. 121558
ማከፋፈያ ክፍል ............... 117343-114770

# የኢ.ሕ.አ.ፓ.መሪ በአሳሽ ጓዶች ተገደለ

( ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት )

ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ የተባለው የኢሕአፓ መሪ ትናንት ከጧቱ በአራት ሰዓት ላይ በአሳሽ ጓዶች የተገደለ መሆኑ ተገለጠ ። የኢሕአፓ የውስጥና የውጭ የፖለቲካ ጉዳይ ዋና ተጠሪ የነበረው ተስፋዬ ደበሳይ ትናንት በአሳሽ ጓዶች የተገደለው እጁን እንዲሰጥ ቢጠየቅ አሻፈረኝ በማለቱ በጥይት ከተመታ በኋላ በመስኮት ዘሎ ለማምለጥ ሲሞክር እንደሆነ ታውቋል ። ከዚሁ ፀረ አብዮተኛ የኢሕአፓ መሪ ጋር በሪሁን ማሪዬ የተባለው አንድ የኢሕአፓ አባል የተገደ ለመሆኑ ተረጋግጧል ።

ትውልዱ ኤርትራዊ የሆነው ተስፋዬ ደበሳይ ኢሕአፓ የተባለውን ፀረ አብዮት ድርጅት ከመሠረቱት አንዱ ሲሆን ፣ ይህ ድርጅት እንደተቋቋመ የውጪ ግንኙነት ኃላፊነቱን ተቀብሎ ሲሠራ የቆየ ነበር ። በዚህም ኃላፊነቱ በአውሮጳ በነበረበት ወቅት የኢትዮጵያን ተራማጆች በመከፋፈል ብዙ የጣረና በአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎችማኅበርን ለማዳከም ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎችፌዴሬሽን የተባለውን የግልገል ፋሽስቶች ቡድን ከመሠረቱት አድኃሪዎች አንዱ ነበር።

ተስፋዬ ደበሳይ የኢሕአፓ የበላይ ተጠሪ ሆኖ በውጭ አገር በቆየበት ወቅት እነመንገሻ ሥዩምን ተራማጅ አስመስሎ በማቅረብና የተማሪዎችን ንቅናቄ በነሱ ጥላ ሥር በማድረግና ... አድኃሪ መሪዎችም ጋር ይፋ የሆነ ግንኙነት በመመሥረት ሲታገል በተራማጅ ተማሪዎች ፊት የተጋለጠና የተተፋ አድኃሪ ግለሰብ ነበር ።

የየካቲት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ከፈነዳ በኋላ ወደ ሀገር ተመልሶ ከኢዲዩና ከኢ- ኤል ኤፍ ጋር ባለው የጠበቀ ግንኙነት የተነሣ የኢሕአፓ የውጭና የውስጥ ፖለቲካ ጉዳይ ዋና ኃላፊ ሆኖ እንዲመረጥ ካደረገ በኋላ ባለፉት ሁለት ዓመታት ይህንን ድርጅት በበላይነት ሲመራ ቆይቷል ።



በአሳሽ ጓዶች የተገደለው የኢ.ሕ.አ.ፓ መሪ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ

ተስፋዬ ደበሳይ በዚሁ በያዘው የመሪነት ቦታ በመጠቀም ከነመንገሻሥዩምና ከኢኤልኤፍ ጋር ባለው የቆየ ግንኙነት መሠረት ይህንን ድርጅት ከነዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድኖች ጋር ለማቈለፍ በግንባር ቀደምነት የታገለና ከሥራም ላይ ያዋለ አድኃሪ ግለሰብ ነበር።

ተስፋዬ ደበሳይ በአሳሽ ጓዶች በተ

በ፫ኛው ገጽ በ፪ኛው ዓምድ ዞሯል

ከ፩ኛው ገጽ ከ፫ኛው ዓምድ የዞረ

ገደለበት ጊዜ ለፀረ አብዮት ተግባሩ የሚያውለው ፩ሺ ብር (አንድ ሺህ የኢ.ት/ ብር) እና ሰባት መቶ የአሜሪካን ዶላር በኪሱ ተገኝቷል ።

ብዙ ሐቀኛ ወጣቶችን አወናብዶ ወደፀረ አብዮት ገደል የከተተው የኢ.ሕአፓ መሪ መገደሉ ለኢትዮጵያ አብዮታውያን እንደ አንድ ድል የሚቆጠር ከመሆኑም ሌላ በዚህ አድኃሪ መገደል ኢዲዩና ኢኤልኤፍ ቀንደኛ ሰርጎ ገብ ያጡ መሆናቸው አያጠራጥርም ።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ኮከብ መሪ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ልክ የዛሬ 38 ዓመት መጋቢት 15 ቀን 1969 ዓ.ም. በፋሽስት ደርግ በተደረገበት ከበባ ከፎቅ ተወርውሮ ሕይወቱን በመስጠት ታሪክ የሠራበት ቀን።

ዶር ተስፋዬ ደበሳይ ለሀገሩና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግንባር ቀደም መሪ ብቻ ሳይሆን መሀል ሆኖ ታገሎና አታግሎ በደሙ ታሪክ የፃፈ ኮከብ መሪ ነበር።

“በአዲስ አበባ ከተማ የቤት ለቤት አሰሳ ለማድረግ እቅድ ወጣ። ደርግ በ1969 ዓ.ም. ለተጀመረው የቤት ለቤት የአስሶ መደምሰስ ዕቅዱ የሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽ/ቤትን በጉያው በተወሸቀው “መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ” (መኢሶን) የበላይ ተቆጣጣሪነት በአዋጅ በማቋቋም በርካታ አሰሳዎችን አካሂዷል።

ከመስከረም 1969 ዓ.ም. ጀምሮ ደርግ በፈለገው ቦታ በፈለገው ጊዜ የቤት ለቤት ፍተሻ (አሰሳ) አካሂዷል። ዛሬ ካዛንችስ አስሰው ከሆነ በሌላ ጊዜ መርካቶን ያምሱታል። እንዲህ እያሉ አሰሳው በተለያየ ቦታ ይካሄዳል።

በመላ አዲስ አበባ በአዋጅ ደረጃ የተካሄዱት አሰሳዎች መጋቢትና ሚያዝያ ወር የተካሄዱት ናቸው። የመጀመሪያው ለሦስት ቀን የተካሄደው ዕሮብ መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ.ም. የተጀመረው ሲሆን ሁለተኛው አርብ ሚያዝያ 28 ቀን 1969 የተካሄደውና መኢሶንም ራሱ የወጠነው ጥቃት ሰለባ የሆነበት አሰሳ ነበር።

በአሰሳው ማንም ከአንድ ቀበሌ ወደ ሌላው መዘዋወር አይችልም። ከአዲስ አበባ የሚያስወጡ ኬላዎች በሙሉ በጥብቅ ጥበቃ ይካሄድባቸዋል። በመጋቢቱ አሰሳ በአብዛኛው የተሳተፉት የደርግ አሳሽ ቡድኖች፣ ቀበሌ ጠባቂዎችና የመኢሶን ካድሬዎች ናቸው። የአሰሳው ዋናው ትኩረት መሣሪያ ነው። አንዳንድ የፓርቲው ሰነዶችም ጠላት እጅ እንዳይወድቁና አደጋ እንዳያስከትል ሁሉም ጥንቃቄ እንዲያደርግ ትዕዛዝ ተሰጥቷል። ሠነዶች በፈታሾቹ እጅ እንዳይወድቁ ከቤት ይልቅ በተለያየ ዘዴ ደጅ ማድረጉ ይመረጥ ነበር። አሳሾቹ እቤት ገብተው ሳጥን፣ ቁም ሳጥን፣ አልጋ ሥር፣ ኩሽና ውስጥ ሊፈትሹ ስለሚችሉ በነዚህ አካባቢዎች ምንም አይቀመጥም።

በአሰሳው ወቅት የቀበሌ መታወቂያ የሌለው ለችግር ይጋለጣል። ተማሪም ለነበርነው ተጨማሪ የትምህርት ቤት መታወቂያ ሊጠየቅ ይችላል። ቀደም ባሉት ድንገተኛ አሰሳ አሳሾቹ ምን እንደሚፈልጉ በደንብ የሚያውቁ አይመስሉምና ለመሸወድና ለማታለል በጣም ቀላል ነበር። የመጋቢቱ አሰሳ ጠንካራና ከበድ ያለ ነበር። በዚህ አሰሳ የመኢሶን ካድሬዎች በመሠማራታቸው፤ በየአካባቢው የሚያውቁትን አስይዘዋል። አስገድለዋል። ፓርቲው ቁልፍ አባላቱን ብቻ ሳይሆን አመራሩን ያጣበት አሰሳ ነበር።

የሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽ/ቤት እና መኢሶን የአስሶ መደምሰስ ዘመቻ በተግባር ለመተርጎም የቤት ለቤት አሰሳ መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ.ም. ተጀመረ። የአብዮት ጥበቃ አባላት፣ ጦር ሠራዊቱ፣ ቀበሌዎች፣ የሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት በተለይም መኢሶንና ሌሎች

በደርግ ዙሪያ የተሰበሰቡ ቡድኖች አባላት በቤት ለቤት አሰሳው ተካፍለዋል። ለሶስት ተከታታይ ቀናት የተካሄደው አሰሳ ሕዝቡ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ እንዳይንቀሳቀስ በወጣ የደርግ ተከታታይ መግለጫ የታገዘ ነበር።

ከኢ.ሕ.አ.ፓ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የተጠረጠሩ ወጣቶችና ሠራተኞች ሁሉ በጅምላ ታሰሩ። በ1969 ዓ.ም. በየካቲት ወር መጨረሻ አካባቢ በርካታ የኢ.ሕ.አ.ፓ አመራር አባላት አዲስ አበባን ለቀው መውጣታቸው ቢታወቅም ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ የአዲስ አበባው የኢ.ሕ.አ.ፓ መዋቅር ውስጥ ያሉ አባላትን በእንዲህ ያለ ቀውጢ ጊዜ ትቶ መሄዱ ለሕሊናው ስለከበደው ለሀገሩና ለሕዝቡ ብሎም ለትግሉ የሰጠውን ሕይወቱን በፍጹም እምነቱ ሊተገብር ማንኛውንም መከራና ስቃይ እራሱን ከፍ ሳያደርግ እንደ ሌሎች የኢ.ሕ.አ.ፓ አባላት አብሮ ሊመክትና ሊታገል ወሰነ።

የኢ.ሕ.አ.ፓ አመራር አባል የነበረው ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ በመጋቢቱ አሰሳ በአሳሾች እጅ መውደቁን ሲገነዘብ ራሱን ከፎቅ ወርውሮ ገደለ። ለኢ.ሕ.አ.ፓና ለአባላቱ ቅስም የሚሰብር መርዶ ሆነ።" *ፍጹም ነው እምነቱ፡ በነሲቡ ስብሐት መስከረም 2007 ዓ.ም.*

ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ በተሰዋ ምሽቱን በኢትዮጵያ ሬድዮ ስርጭት ዜናው ሲቀርብ በማግስቱ መጋቢት 16 ቀን 1969 ዓ.ም. ከላይ እንደተቀመጠው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ትኩስ ዜና ሆኖ ወጥቷል። አዎ የተስፋዬ በፋሽስቶቹና ባንዳዎች እጅ መውደቅ ትልቅ ደስታቸው ነበር። ደርግ ኢ.ድ.ዩ፣ ሻቢያ፣ ገንጣይ፣ ግልገል ፋሺስት፣ የ CIA ሰላይ፣ አድኃሪ ወዘተ እያለ ንፁሃንን መወንጀልና መግደል መለያው ነበርና የወጣው የፋሺስቶች ቱልቱላ አዲስ ባይሆንም የኢ.ሕ.አ.ፓ መሪ ተስፋዬ መሰዋት በእርግጥ ለፓርቲውና ለአባላቱ ብሎም ለሚታገልለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅስም ሰባሪ መርዶ ነበር።

በ «ያ ትውልድ ተቋም» ዝክረ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ልዩ እትም ስለ ጀግናው ታጋይ አንድዬ ልጁንና እናቷን ጨምሮ ቤተሰቡና ጓደኞቹ በሚያዝያ 2005 ዓ.ም. ሜይ ዴይን አስመልክቶ በ«ያ ትውልድ ተቋም» ፓል ቶክ ክፍል አዘጋጅተን የነበረውን የፓል ቶክ ውይይት መነሻ በማድረግ ስለ ዶር ተስፋዬ ደበሳይ የሰጡትን ዘርዘር አድርገን አቅርበናል።

### *ወ/ሪ ሐምራዊት ተሰፋ*

"ያደኩት አዲስ አበባ ነው በአራት ወሬ ነው አባቴ የሞተው። ከዛ በኋላ እናቴ ፍቅርተ በዘጠኝ ወሬ ነው ወደ ዕቡህ ትግል ገብታ የተለየችኝ ። ያው ሊገድሏት ሲሉ። እኔን ያሳደገኝ የእናቴ ወንድም አጎቴ ተስፋ ነው። 'ይህችን ልጅ ቢያውቁ ይገድሏታል' ብሎ በጣም ይፈራ ነበር። ስለዚህ እኔ እራሴ እንዳውቅ አይፈቀድም። ይፈራ ነበርና ካወቁ ይገድሏታል ብሎ ስለሚያስብ። ከዚያ በኋላ ግን ዘመዶቼ እየመጡ ያዩኛል። የተስፋዬ ዘመዶች ማለት ነው። ከሱ ዘመዶች የአክስቴ ልጅ ጽጌ ነበረች አንደኛ ጠያቂያችን። ዘመድ እያሰባሰበች የምትመጣው እሷ ነበረች። ለነሱም ያስጠነቅቃቸዋል 'ምንም ነገር እንዳትነግሯት' እያለ። አብሬ ያደኳቸው ሁለት ወንድሞች አሉኝ በጣም ስለሚወዱኝ ስለሚሳሱልኝ 'እነዚህ ሰዎች ማናቸው?' ብዬ እጠይቀው ነበር። እና ስጠይቀው 'የፍቅርተ ጓደኛ ነች' ይለኛል።

በተደጋጋሚ እየመጡ ይጠይቁኛል፡ ይወዱኛል። ምን እንደነበር አላውቅም። ለመጀመሪያ ጊዜ ያወቅሁት ኢሕአፓ ሦስት ዓመቱ ሳለ አያቴና አክስቴ ሲያወሩ እሰማቸዋለሁ። የፍቅርተ እናትና እህቷ ማለት ነው። ያወራሉ 'ጽጌ መጥታ ነበር' ይሏታል

'የትኛዋ ጽጌ' ትላቸዋለች ስትላቸው 'ያቺ የሐምራዊት አክስት ልጅ' ይሏታል

እንደዚያ ሲሏት ያኔ በቃ ደነገጥሁ። ሁሉ ነገር ጥርጣሬ ውስጥ ከተተኝ። እንዴት የሌሎቹን ስም ጠርተው የእንትና አክስት አላሉም ብዬ ሌላ ነገር ተገጣጠመብኝ። እና በቃ እነዚህ ሰዎች እንዴት በፍቅር እንደሚመለከቱኝ፣ እንደሚሳሱልኝ እኔጋ በተደጋጋሚ የሚመጡት ሁሉ መጣብኝ፣ ተገናዘበብኝ ማንንም አልጠየቅሁም ግን በአእምሮዬ ላይ አንድ ነገር ጫረብኝ። በዚያ ሰዓት በጣም ግራ ገባኝ። ሁሉ ነገር ዝብርቅርቅ ስሜት ተሰማኝ። ሌላ አባት አለኝ? የሚለው።

እዚህ ሀገር አሜሪካ ስመጣ ደግሞ በመጣሁ በማግስቱ ቁጭ አደረገችኝና እናቴ ስለ ተስፋዬ ለመጀመሪያ ጊዜ ነገረችኝ። ስትነግረኝ በውስጤ በጣም እጅግ በጣም ደንግጬሃለሁ። ምክንያቱም ማላውቀው ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲነገረኝ ነውና። በጣም ደንግጬሃለሁ በፊቴ ግን ምንም ነገር ላሳያት አልፈለኩም። ምን ልበላችሁ በጣም በጣም ይረብሻል። ከዛ ምንም ነገር እንዳትቀጥል ፈለግሁ። ቶሎ ዘጋኋት። ነገሩ ሁሉ አስፈራኝ ለእኔ እጅግ ፈታኝ ጉዳይ ነበር። ታሪኬን እራሱ ለመቀበል ማንነቴን ለማወቅ። ዘመዶቼን እራሱ ለረዥም ጊዜ ልቤን ከፍቼ አልቀበላቸውም ነበር ። ሌላ ሰው ነሽ ስባል በጣም ግራ አጋባኝ ማለት ነው።

ብዙ ሰዎች አሉ እናት አባታቸውን ሳያውቁ ያደጉ እኔ በዚህ በኩል በጣም እድለኛ ነበርኩኝ። ያሳደገኝ የእናቴ ወንድም የተንከባከበኝ እንደ አባት ነው። ወንድም ለማለት ይከብደኛል። እንደ አባት የማውቀው እሱን ስለነበር ሲነገረኝ ሌላ ማንነትን ፍለጋ ማሰብ እጅጉን ይከብዳል። እውነት ለመናገር የተስፋዬን ታሪክ ለማወቅ እንኳ ዝግጁ አልነበርኩም። ምክንያቱም ያላሰብኩት አዲስ ነገር ነው የሆነብኝ። በፍራቻ ላይ ነበርኩኝ። ሆኖም እያደኩ ስመጣ የማንነቴን ጭላንጭል እየሰማሁ ስመጣ በማንነቴ በጣም መኩራት ጀመርሁ። ከምሰማው፣ ከምጠይቀው፣ እኔ እራሴ ካነበብኩት እየሰማሁ ስመጣ እራሴ የሱ ልጅ መሆኔን እኮራበት ጀመር። የሱ አባትነት ሁልግዜ በውስጤ ይጎላ ጀመር። ይመላለስ ጀመር። የወለደኝ አባቴ ነው። የእኔ ማንነቴ ነውና። በራሴ ማንነት አንዱን ለማግኘት ሌላውን ማጣት እንደሌለብኝ አመንኩ። በመሆኑም በሙሉ ልቤ ተቀበልኩት ኮራሁበት።

መጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ስሄድ የዛሬ አምስት ዓመት አካባቢ ካሳደገኝ አባቴ ጋር ነበር አብረን የሄድነው። 'ኢያትሽን የተስፋዬን አባት አቦይ ደበሳይን ለመጀመሪያ ጊዜ እያቸው፣ ዘመዶችሽን እያቸው' ብሎኝ ለመጀመሪያ ጊዜ አብረን ሄድን። ስሄድ መጀመሪያ ፈርቼ ነበር። ተስፋዬ እተወለደበት ሀገር ስሄድ የማላውቃቸው ሰዎች ናቸው፣ እንዴት ነው የሚሆነው ብዬ በጣም ግራ ገብቶኝ ነበር ። ሄድኩኝ ደረስን። እዚያ አካባቢ ስደርስ በጣም ማልቀስ ጀመርኩ። ለምንድነው ያለቀስኩት ጦርነት ሲባል ከሩቅ ቦታ ሆነን ስናየው ሌላ ቦታ ነው የሚመስለን፣ ሌላ ቦታ ያለ ጦርነት፣ ሌላ ሰዎች፣ ከሩቅ ስትሰማው ሁልጊዜ ሌሎች ሰዎች ነው የሚመስለን። ልክ እሱ መንደር ስንደርስ 'እየሁላችሁ ይህ እንዲህ ነው' እያለ

*አካባቢውን የሚያሳየን ገለፃ የሚያደርግልን ሰው አብሮን ነበር። 'ከዚህ ቦታ እንደዚህ ሰዉ ተፈናቅሎ፣ ከዚህ ቦታ ያሉት ልጆችና ሽማግሌዎች ሁሉ ሄደው' እያለ በቅርብ በነበረው ጦርነት ማለት ነው ያሳየን ነበር። በሻቢያና በኢሕአዴግ መካከል በነበረው ጦርነት። የሰዉን ጉስቁልና ሳይ፣ ሁኔታውን ሲያሳየኝ በጣም አስለቀሰኝ። እዚያ ቦታ ሆነህ በአካል ስታየው ያለው ስሜትና በርቀት ምትሰማው ይለያያል።* ***<u>በደንብ እንዲገባህ እዛው ሆነህ ስታይ ይመረጣል።</u>*** *በጦርነት የሰው ጉዳት የሚገባህ ጥሎ የሚያልፈውን አሻራ በቦታው ስታየው ነው። በጣም አሳዘነኝ። አያቴ ያሉበት አካባቢ በጣም ድሃዎች ናቸው። እንደደረስኩም የተስፋዬን አባት አያቴን አገኘኋቸው። ለረዥም ጊዜ እጄን ይዘው ትክ! ብለው አዩኝ። ምንም ነገር አልተናገሩም፣ ዝም ብለው አዩኝ። ከዛም በኋላ አብረን ባለንበት ሁሉ እጄን ሊለቁ አልፈለጉም። ታዲያ እንደልብ እንዳያወሩኝ ቋንቋ አንግባባም ነበር። እሳቸው አማርኛ አይችሉም እኔ ደግሞ ትግርኛ አልችልም። ግን በቃ ስለ ኢሕአፓ ፍቅር አላቸው፣ ስለነሱ ያወራሉ፣ ያኔ በኢሕአፓ ጊዜ ሰዎች እንዴት እነሱጋ ይመጡ እንደነበር የነበራቸውን ትውስታ ያወራሉ። በቃ! ለኢትዮጵያ እጅግ ፍቅር አላቸው። አማርኛ ስለማይችሉ የሚነግሩኝ ልጆች እያስተረጎሙልኝ ነው። 'አይ ቂቋ ቋቋ'' ይላሉ። 'እኔም የልቤን ማውራት አልችል፡ አንቺም የልብሽን ማውራት አትችይ' ይላሉ።*

*ምን አሉኝ ያን ጊዜ 'ተስፋዬ መሞቱን ሳውቅ ሸፍቼ ነበር' አሉኝ። መሞቱንም እንደማንኛውም ሰው በሬድዮ ነበር የሰሙት። ከሸፈቱ በኋላ ግን ብቻቸውን ምንም ማድረግ ስለማይችሉ ተመልሰው መጡ። አንድ ወንድ ልጃቸው ነበር። ስለ ልጅነቱም ስጠይቃቸው 'በጣም ጎበዝ! ጎበዝ! ተማሪ ነበር' አሉኝ። በጣም ጠንካራና ብርታት ያላቸው ናቸው። ይቀልዳሉ፣ ይኮምካሉ፣ አማርኛ የሚያውቋት አንድ ናት 'ገና…ና…ገና አዲስ አበባ ይታደሳል ገና' ይላሉ። እየደጋገሙ ይሏት ነበር። እና በጣም ደስ አለኝ። የአባቴን አባት አየሁ ማንነቴን አወቅሁ፣ በአባቴ ኮራሁበት። እሳቸውም እንዳዩኝ ማመን አቃታቸው ዓይናቸው ከዓይኔ ላይ አልነቀል አለ። 'ልጄ መጣሽልኝ' አሉ። ደስታቸውን መግለጫ ቃል አጡ። ገጽታቸው ለእኔ የሚነበብ ነበር። ይዘፍኑም ነበር 'ተስፋዬ…ና…ተስፋዬ…ና…ና… ልጅህ መታለችና' ይላሉ ይዘፍናሉ። እስካሁን ድረስ አልወጣላቸውም። ሌላ ደግሞ ስለ ትውልድ ዝርያ በጣም ነገሩኝ 'እገሌ እገሌን ወለደ' እያሉ አስረዱኝ። በደንብ ያውቃሉ። ከመለያየታችን በፊት 'መታወቂያዎን ስጡኝ' አልኳቸው እሷኑ ያለቻቸውን አውጥተው ለማስታወሻ ሰጡኝ። ይዣት መጣሁ። በጣም ደስ የሚል ወቅት ከአያቴ ጋር አሳለፍኩኝ። ደስታዬን ጨመሩልኝ፡ ኩራቴን ተንከባከቡልኝ። ውስጣቸው የሞላውን ተስፋና ፍቅር አካፈሉኝ።*

*ከቅርብ ጓደኛው/ዘመዱ የተስፋዬ የግል ማስታወሻ አገኘሁ። እነሱ ጋ ተቀምጦ ነበርና ሁሉም ሰነዶች ሲቃጠሉ ተደብቃ የተረፈችው የግል ማስታወሻው ነበረች። ከተሰጠኝ የተስፋዬ የግል ማስታወሻ እንደተረዳሁት ተስፋዬ ለሰው ተቆርቋሪ አዛኝና ሀሳቢ እንደሆነ ነው። ለሌሎች ለመድረስና ለመቆም ስላለው ፍላጎት፣ ፍላጎቱን ለማሳካት ያለውን ጥረት በአብዛኛው ከራሱ ጋር የሚያወራውን አነበብሁ። ይህ በአማርኛ የፃፈው የግል ማስታወሻው ይበልጥ ስለማንነቱ እንዳውቅ እረድቶኛል።" ሐምራዊት ተስፋ የዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ልጅ።*

### *ወ/ሮ ፍቅርተ ገ/ማርያም*

"የተስፋዬ ታሪክ የፍቅር ታሪክ ብቻ አይደለም። የተስፋዬ ታሪክ የትግል ታሪክ ነው። በአብዛኛው በነበርንበት ጊዜ የማውቀው ከትግሉ ይልቅ እኔና እሱ ባለን ግንኙነት ነው የማውቀው። ስለ ተስፋዬ ብዙውን ሊናገሩ የሚችሉት አብረውት በአንድ ኮሚቴ ውስጥ የሠሩት፣ አብረውት አሠራሩን ያዩ ሰዎች ናቸው። በዚያ ጊዜ ዴሞክራቲክ ማዕከላዊነት (Democratic Centralism) ነው አሰራሩ። ብዙውን ጊዜ በግል ጨዋታ ውስጥ ስለ ትግሉና ስለ አሰራር የሚወራ ጉዳይ የለም። ተስፋዬ ደበሳይ ጋር የተገናኘነው ስዊዘርላንድ ነው። የተዋወቅነው የተማሪ ማህበር በርሊን ውስጥ የነበረ ስብሰባ ላይ ነው 1974 እ.ኤ.አ። ስዊዘርላንድ አብረን እንኖር ነበር። ለአንድ ዓመት ያህል አብረን ኖረናል። የማውቀውን ልናገርና ተስፋዬ ደበሳይ በጣም ትሁት፣ ቀና፣ ዶክተር ተስፋዬ መባል የማይፈልግ ሰው፣ እራሱን ደብቆ የኖረ ሰው ነው። ለተስፋዬ አንድ የሚያሳዝን ወሬ ስታወሩት ዕምባው ነው ግጥም የሚለው። ትሁት፣ ደግ፣ በጣም ርዕሩህ፣ የሱን ፍላጎቶች በሙሉ ለሰው አሳልፎ የሚሰጥ። አንድ ትንሽ ልጅ ነው የሚመስለው አኗኗሩ፣ አለባበሱ፣ አኗኗሩ፣ አነጋገሩ። ለሰው ነው ቅድሚያ የሚሰጠው። አንድ ነገር ሰው ማውራት ሲጀምር የማያውቅ ነው የሚመስለው ተስፋዬ። ከሌላ ሰው መስማት ላይ ነው የሚያተኩረው። ነገር ግን አንድ ነገር በሚጠየቅበት ጊዜ ወይም እንዲህ ሊደረግ ነው ሲሉት ተስፋዬ ወዲያውኑ እንደዚህ መሆን አለበት አይልም። ተስፋዬ አንተ እራስህ ያንን ጥያቄ እንድትመልስ ዙሪያውን ይዳስሳል። እየዳሰሰ…እየዳሰሰ… እሱ እንዲህ ነው ብሎ ከመመለሱ በፊት አንተ እራስህ ጥያቄውን በራስህ እንድትመልስ የሚያደርግህ ሰው ነው። ይገርመናል ያን ጊዜ በትግሉ ጊዜ ጓዶቹን አብረውት ሲሰሩ የነበሩት ሰዎች የሚያውቁት እሱን ትዕግስተኛ በመሆኑና ዐዋቂ ነኝ የማይል ሰው ግን አንተው እንድታውቅ አንተው እንድትመልሰው 'ይህንንስ አይተኸዋል? በዚህ በኩልስ ተመልክተኸዋል? እንዲህ ቢሆንስ?' እያለ የሚመልስ ሰው ስለነበረ እኔ ከሁሉም በላይ ትዕግስተኛነቱና የዕውቀቱ ደረጃ እስካሁንም አላየሁም። በአለችኝ ትንሽ የእውቀቴ ጭንቅላት ነው የማወራው። እንደ ተስፋዬ ደበሳይ ሰው አይቼም አላውቅም፤ እውቀትም ያለው እንደዚያ የማውቀው ሰው የለምና ሚኮራበት ኢትዮጵያዊ ነበረ። የሞተው ባመነበት ነው። አያሳዝንም። ለምን? ካልሆነ መሞት የሚፈልገው እንደዚያ ነበርና። <u>ብዙ ነገር አውርሶ ያለፈ ሰው ነው</u>። ታሪኩም ወደፊት በሰፊው የሚፃፍለት ነው። እኔ በዚህ ነው ተስፋዬን የማውቀው" *ወ/ሮ ፍቅርተ ገብረማርያም የዶር ተስፋዬ ደበሳይ ባለቤት የነበሩት።*

### *ወ/ሮ ካሰች ደበሳይ*

"እኔ ብዙ የማውቀው ባይኖርም የምወደው ወንድሜ ነው። ለሕዝቡ ሲል ለጭቁን ሕዝብ ሲል ሕይወቱን ያሳለፈ ነው። ለትንሽ ጊዜ ነው ከሱ ጋር የነበርኩት። በትምህርቱ ጎበዝ የነበረ ነው። ለሰው የሚያስብ፣ ከድሃ ቤተሰብ ተወልዶ ተምሮ ለቤተሰቤ ሳይል ለሁሉም ድሃ ሕዝብ፣ ለሁሉም ጭቁን ሕዝብ ሲል የሞተ ሰው ነው። እኔ ሳውቀው ጥሩ አስተሳሰብ ያለው መጽሐፍ ከእጁ የማይለቅ ሲበላም ሲቀመጥ በጣም ያነብ ነበር።

አዲስ አበባ ልጅ ሆኜ ነበር የሄድኩት ወደ ውጭ ከመሄዱ በፊት ለሁለት ዓመት አብረን ነበርን። እቤት የሚመጡ ወንዶች ነበሩ ዘርዑ ክሽን ይመጣ ነበር። ያክስቴ ልጅ ንጉሴ ያን ጊዜ በአንድ ወር ልዩነት የሞተው ይመጣ ነበር። ወንድምሽ ሞተ ሲሉኝ ያኔ ወሎ ውስጥ ንጉሴን መስሎኝ ያን ጊዜ እሱ አልሞተም እያልኩ ስከራከር ከዚያ የሚያውቁ ሰዎች ወስደውኝ ሌላ ቤት እያስገቡ በቃ እነዚያን ሰዎች እንዲሄዱ ያደርጉ ስለነበር የንጉሴንም መሞት ስሠማ ከሌሎቹ ጋር ጭቅጭቅ እፈጥር ጀመር በቃ! መርዶ ስለሆነ " *ወ/ሮ ካሰች ደበሳይ እህት*

## *ወ/ሮ ጽጌ ፍሱሕ*

"ተስፋዬን ለጥቂት ጊዜ ነው ያየሁት። ባየሁት ወቅት ትዝ የሚለኝ መጽሐፍ አንባቢነቱ ነው። ሐምራዊትን እንደአባት ሆኖ ያሳደጋት የእናቷ ወንድም አቶ ተስፋ ገ/ማርያም በጣም ሰው አክባሪ ምንም ዓይነት የሰው ልዩነት የማያደርግ ሰው እንደነበረ፣ ሐምራዊት ዛሬ ለደረሰችበት ደረጃ ያደረሰ ሰው መሆኑን ልናገር እፈልጋለሁ። አሥመራ የምትኖር የዶክተር ተስፋዬ እህት ብስራት አዲስ አበባ መጥታ ሐምራዊትን ለማየት 'ይዘሽኝ ሂጂ' ስትለኝ 'ስታያት ምንም እንዳትረበሺ' ብዬ ይዣት ብሄድም ስታገኛት እያለቀሰች እንደተረበሸች ለመናገር እፈልጋለሁ።" *የዶር ተስፋዬ የአክስት ልጅ ወ/ሮ ጽጌ ፍሱሕ*

## *ወ/ሮ አስቴር ደበሳይ*

"አስቴር ደበሳይ እባላለሁ። በምታደርጉት ታሪክ ማሰባሰብ እኔ በጣም ደስ ብሎኛል። በዚያን ሰዓት በጣም ልጅ ነበርኩ የፋሲካ ጊዜ ማታ እቤት መጥቶ ኑሯችንን ጠይቆ ስለ ትምህርታችንም 'አይዟችሁ ጐበዝ ተማሪ ሆናችሁ ተማሩ' ብሎን እንደሄደ አስታውሳለሁ። ግን አንድ አጎታችን 'አንተ የተማርህ ነህ፣ ሰርተህም ደህና ገንዘብ ታገባ ይሆናል እና ቤተሰቦችህን ለምንድነው ጥሩ ቦታ ላይ የማታደርሳቸው?' ብሎ ሲለው 'አይ እኔ ለቤተሰቦቼ ብዬ አይደለም። እኔ ለቤተሰቦቼ ካደረግሁ ሌላውስ ቤተሰብ? እኔ የማስበው ለቤተሰቦቼ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም፣ ለሌላውም ቤተሰብ ነው' ብሎ ሲመልስለት አስታውሳለሁ።" *ወ/ሮ አስቴር ደበሳይ እህት*

## *አቶ ግርማይ ተስፋ ጊዮርጊስ*

"ተስፋዬ እንደ አንድ ሰው፣ እንደ አንድ ታጋይ፣ እንደ አንድ መሪ ብቻ አይደለም የሞተው፤ ብዙ መሪዎች እንዳለቁ ነው የሚታየው። ምክንያቱም በላቀ ዕውቀቱና ትዕግስቱ የተለያየ አመለካከትና ልምድ የነበራቸው ታጋዮችን አስተባብሮ የመምራት ችሎታ የነበረው እሱ ነበር። ተስፋዬ እጅግ ዴሞክራት ነበር። ይህ ዴሞክራት የመሆን ነገር ዝም ብሎ የመጣ አይመስለኝም። የተወለደበት የኢሮብ ብሔረሰብ (በትግራይ ውስጥ የሚገኝ አናሳ ብሔረሰብ ነው) እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ 1935 እ.ኤ.አ. ማለት ነው የራሱን መሪዎች በራሱ የሚመርጥና በመረጣቸው መሪዎች የሚተዳደር ማህበረሰብ ነበር። በኢሮብ በየመንደሩ ምርጫ ይካሄዳል። በዚህ ዘዴ የተመረጡ ወኪሎች አማካኝ ቦታ በመላክ ጠቅላላ ምርጫ ይካሄዳል። የተላኩት ወኪሎች አንድ ቦታ ይሰበሰባሉ ከዚያ በማጣራት ወደ ሁለት ያወርዱና

ሰዎቹ ቅጠል ይታደላቸዋል። ቅጠሉን እሚመርጡት ሰው ጋ ካስቀመጡ በኋላ ያ ቅጠል ይቆጠርና ብዛት ያገኘው ይመረጣል። በዚህ መልክ የተመረጠው ለተወሰነ ዓመታት ያገለግላል። የተወሰነው የአገልግሎት ጊዜ ሲገባደድ በተመሳሳይ መልኩ ሌላ ምርጫ ይካሄዳል። ተስፋዬ ከዚህ ዓይነት ኅብረተሰብ የተወለደ ነው። ሁለተኛ በጣም ከድሃ ቤተሰብ ስለተወለደ የድሃ አኗኗር ይገባዋል። ሁሉም መሪ የድሃ ችግር ምን ያህል እንደሆነ ሊያውቅ አይችልም። እራሱ ድህነትን ያለፈበት ስለሆነ በጣም ዴሞክራት ያደረገውና የሕዝብ ወገን ያደረገው። ለምሳሌ አንድ ጊዜ ስዊዘርላንድ በነበረበት ጊዜ ሀገር ቤት ሥራ ላይ ቆይቶ ከወጣ በኋላ እኔ ጣሊያን ሀገር ነበርኩና ወደዚያ መጥቶ መቸም በእግር እንሂድ እያለ ያስቸግርሃል ከተማ ውስጥ በእግር እየሄድን በመሃል አንድ ነገር አልኩት። እንግዲህ አዲስ አበባ ሥራ በያዘበት ጊዜ በወቅቱ ሥራ የያዘ ሰው መጀመሪያ ወላጆቹን ይረዳል ነው የሚባለውና ሥራ ይዞ ቤተሰቡ ላይ የኑሮ ለውጥ ስላልታየ ምን ዓይነት ጨካኝ ነው እረስቷቸዋል እኮ እያሉ የሚያወሩ ሰዎች ነበሩና ይህንን ነገርኩት። 'ሰው ምን እንደሚል ታውቃለህ ወይ?' አልኩት። 'በጣም ጨካኝ ነው፣ ጥሩ ሥራ እያለው ወላጆቹን እህቶቹን አይረዳም ብለው እንደሚያሙህ ታውቃለህ ወይ?' አልኩት።

'አውቃለሁ ቢሉም እውነታቸውን ነው ግን አባቴና እናቴን ብረዳ አንቱ አለ፣ እክስቴ አለች፣ ከዚያ ቀጥሎ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እናቴና አባቴ ስለሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰርቶ የሚኖርባት ሀገር ለማቋቋም ከሚጥሩ ጋር ታግለን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ መፍትሄ ለመፈለግ ምርጫ ስለወሰድኩ ነው እንጂ' ብሎኝ ነበር። ስለዚህ ምን ያህል ለሕዝብ እንደሚያስብ አስተያየቱ ከበቂ በላይ ይመስለኛል።

እኔ መጀመሪያ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ስብሰባ የተሳተፍኩት እ.ኤ.አ. በ1973 ዓ.ም ነበር አውሮፓ ሀኖቨር እተባለ የጀርመን ከተማ ውስጥ ሂጄ። በተማሪው ንቅናቄ ውስጥ ያኔ በጣም መጥፎ ጊዜ ነበር ትልቅ ንትርክ የነበረበት ጊዜ ነው። ምክንያቱም መኢሶንና ኢሕአፓ በሚስጥር ተቋቁመው ስለነበር የመኢሶን ሰዎች የተማሪውን ንቅናቄ ወደ ራሳቸው ለመውሰድ የኢሕአፓ ወገን ደግሞ ወደ ኢሕአፓ ለመውሰድ መሪዎቹ የሚጨቃጭቁበት ጊዜ ነበረ። በዚህ የመጀመሪያዬ ስብሰባ በጣም ደነገጥሁ፣ ሌሎችም እንዲሁ። ከመኢሶን ወገን አንድ ሰው ሲናገር የኢሕአፓ ወገኖች ይረብሹታል። ዑ ዑ እየተባለ ቤቱ በጣም ይረበሻል። የኢሕአፓ ሰው ሲናገር ደግሞ በተቃራኒው ያሉት መኢሶን ወገኖች ይረብሹታል። በኋላ ዶክተር ተስፋዬ ተነሳ አታምኑም ቤቱ ውስጥ ዝምብም ያለ አይመስልም፣ ጭጭ ብለው ነው የሰሙት። የተፈጥሮ ስጦታ ነበረው እሱ ሲነሳ በጣም ተናጋሪ ሆኖ አልነበረም ከሱ ሚበልጡ በጣም ተናጋሪዎች ነበሩ። ነገር ግን መጀመሪያ የሚናገራቸው ቃሎች አንድ ቃል ሲወረውር ብዙ ነገሮችን የሚገልጹ ቃሎችን ያውቃልና በጣም ገርሞኛል። እንደዚያ ይረበሽ የነበረው ቤት እሱ ሲነሳ ጭጭ ብለው ሰሙት። እስኪጨርስ ድረስ አንድም የረበሸው አልነበረም። እንዲህ ዓይነት ተሰጥዎም ነበረው። በንግግሩም ስድብ የሚባል ነገር ከአፉ አይወጣም። ቁም ነገሩ ላይ ብቻ ነው የሚያተኩረውና ይሄ አንድ አጋጣሚ ነበር።

በስብሰባዎቹ መካከል በአሉ የዕረፍት ጊዜዎች የኢሕአፓ ደጋፊ ኢሕአፓ ጋ የመኢሶን ደጋፊ መኢሶን ጋ ነበር የሚታየው። ዶር ተስፋዬ ደበሳይ ግን ከኃይሌ ፊዳ ጋር ወይ ከሌላ የመኢሶን ሰዎች ጋር ነበር የሚታየው። ተስፋ አይቆርጥም። ሁል ጊዜ ወደ አንድ መሄድ 'ሁላችን አንድ ህዝብ ለአንድ ህዝብ ስለሆንን አብረን መስራት እንችላለን' የሚል አስተሳሰብ ስለነበረው ሁልጊዜ በውይይት ያምናል። 'የሰው መጥፎ የለውም የተሳሳተ እንጂ' የሚል አካሄድ ስለነበረው ሁል ጊዜ ሰውን ለማረም ቀርቦ ማወያየት ማናገር ሲሞክር እንጂ ሰውን ሲያጥላላ አይታይም ነበር።

ሌላው እሱ የተሰዋበት ቀን አጋጣሚ ሆኖ እኔ በነበርኩበት ቦታ የተገኘ የኢሕአፓ ፖሊት ቢሮ አባል የነበረ ሰው ነበረና ያ መጥፎ ዜና ከሰማን በኋላ ምን አለኝ 'ኢሕአፓ አሜሪካ ተነስቶበት፣ ሶቭየት ህብረት ተነስቶበት፣ ጠባብ ብሔረተኞች ተነስተውበት ኢሕአፓ ምንም ይሆናል ብዬ ጠይቄ አላውቅም ከተስፋዬ በኋላ ግን የምናውቀው ኢሕአፓ አይኖርም' አለኝ። በጣም እያለቀሰ ነው። አለ አሁንም በሕይወት እና 'ከተስፋዬ በኋላ ኢሕአፓ እንደ ኢሕአፓ የምናውቀው ኢሕአፓ አይኖርም ደነገጥሁ።' ብሎኝ ሲያወራ አስታውሳለሁ።

በአዲግራት የ7ኛና 8ኛ ክፍል ተማሪ እያለ በዚያ ወቅት አንድ ተማሪ አይደለም የሚመስለው። ሁሉም ሰው ዘንድ 'ምን ዓይነት ሰው ነው ይሄ ከየት ተፈጠረ' ዓይነት ስሜት ነበር ያሳደረው። አንድ ሰው ነበሩ እዚያ በጣም ታዋቂ ናቸው 'እኔ በሕይወቴ የዚህን ልጅ መጨረሻ አይቼ ብሞት ሌላ አልፈልግም ነበር።' ሲሉ አስታውሳለሁ። ለአሁኑ ትውልድ ግራ ሊገባ ይችል ይሆናል ያን ጊዜ አዲግራት ከተማ አንድ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ቢገኝ ትልቅ ነገር ነበር። በዚያ ጊዜ እሱ ታይም መጋዚን (Time)፣ ኒውስ ዊክ (News Week) ዓይነቶችን ይዞ ይታያል። ከየት እንደሚያመጣው እስካሁን ድረስ ሚስጥር ነው። በጣም አንባቢ ነበረ። ሌላ አንድ የአዲግራት ካቶሊክ ትምህርት ቤት ዴሪክተር የነበሩት ዶክተር አባ ወልደማርያም ይባላሉ ቄስ ናቸው፤ ወደ አሊቴና ሲዛወሩ መፃሕፍት አንድ መጋዘን ክፍል ውስጥ ትተው ነበር የሄዱትና ተስፋዬ ይሄንን ወሬ ሲያገኝ ቁልፉን ፍቃድ ጠይቆ ገብቶ እዚያ የነበረ መጽሐፍ አንድ በአንድ እያወጣ ያነበው ነበር። ሌሎች እንዲህ ሲያደርጉ አይታዩም። በአንባቢነት እንደ ተስፋዬ ዓይነት አንባቢ አለ ብዬ እስካሁን ድረስ ለማመን ያስቸግረኛል።

የካቲት እንቅስቃሴ እንደተነሳ የጠቅላይ ሚንስቴር አክሊሉ ሀብተወልድ ወርደው ልጅ እንዳልካቸው የተተኩበት አካባቢ ነው። አንድ ጽሁፍ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌደሬሽን ስም ለማውጣት ታስቦ ሲያወጡ እሱ መንደርደሪያ (outline) አውጥቶ ለአንድ ሰው ታይፕ እንዲያደርግ ይሰጠዋል። በዚህ መካከል ሰው ቁጭ ብሎ ያወራል። ሌላ ሰው አንድ መጽሐፍ ይዞ መጣና ተስፋዬ 'እስኪ ልየው' ብሎ ወሰደና ገለጥ ገለጥ ያደርገዋል። በግማሽ ሰዓት ውስጥ 'አይ ጥሩ መጽሐፍ ነው' ብሎ ሲዘጋ መልሶ አንድ ሰው 'እንዴ ሳታነብ እንዴት ጥሩ መጽሐፍ ትላለህ' ይለዋል ሌላ ተስፋዬን በደንብ የሚያውቅ ሰው 'ተስፋዬን አታውቀውም ማለት ነው አንብቦታል' ይለዋል። የተለያየ የንባብ ልምድ ስላለው ያቺ መጽሐፍ በግማሽ ሰዓት ውስጥ ጨርሷታል። ይህንን አስታውሳለሁ።

እኔም ሆንኩ ተስፋዬ ትምህርት ቤት የገባነው ዘግይተን ነው። ሁላችን አምስት ዓመት ወይ ስድስት ዓመት ሲሆነን ትምህርት አልጀመርንም። ገጠር ነው በጣም ኋላ ቀር ገጠር። በዚያ ጊዜ ትምህርት ቤት የለም። እኔ እራሴ ሌሎች ኢለመንተሪ በሚጨርሱበት ወቅት በ11 ዓመቴ ነው ትምህርት የገባሁት። ተስፋዬም እንድሁ በተመሳሳይ ዕድሜ ነው ወደ ዘመዱ ሄዶ ትምህርት ቤት የገባው። ግን ተስፋዬ ትምህርት ቤት ከገባ በኋላ ከአለው ልዩ ችሎታ አንፃር በአንድ ዓመት ሁለት ክፍሎች እየዘለለ ነው የተማረው። በአጭር ጊዜ በስድስት ዓመታቸው ትምህርት የጀመሩት ጋ ደረሰባቸው። በአጭሩ ልዩ ተማሪ ነበር።“ *አቶ ግርማይ ተስፋ ጊዮርጊስ፡ የዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ አብሮ አደግ ጓደኛ*

## *አቶ በየነ ገብራይ ተስፉ*

“የሠራዊቱ ህግና ደንብ በጣም በጣም አስፈሪ ነበር። ሁሉም ሰው ቅጣቱ ከከባድ ቅጣት እስከ ሞት የሚል ነው የነበረው። በዚያ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የነበረውን የሠራዊቱን ሕግ ተስፋዬ ደበሳይና ስሙን ማስታወስ ያቃተኝ ሁለተኛው የኢሕአፓ አመራር አባል ወደ ሠራዊቱ በመጡበት ወቅት የሠራዊቱን ደንብ ያሻሻሉበትን ሁኔታ አስታውሳለሁ። እነሱ ያንን ማሻሻል ካደረጉ በኋላ ሠራዊቱ በኮሚቴ መመራት ጀመረ ማለት ወታደራዊ ኮማንድ የሚል ባልሳሳት አምስት አባላት ያሉት አመራር አካል ተመሠረተ። ተስፋዬ መጥቶ ከተሻሻለው ደንብ ውስጥ ‘በሠራዊቱ ውስጥ በጤና ምክንያትም ሆነ የሜዳውን ውጣ ውረድ መከራን አንድ አባል አልችልም ካለ/ካለች መሰናበት ይችላል/ትችላለች’ የሚል ይበልጥ ዴሞክራቲክ በሆነ መልኩ ሕጉ መስተካከሉን አስታውሳለሁ።

ከተስፋዬ ጋር ዝምድና እንዳለን ይታወቃል፤ ሆኖም ግን ከተስፋዬ በምንም መልኩ በድርጅታዊ ሥራ ከሚመለከትህ ውጭ ምንም ዓይነት ነገር ከተስፋዬ ልታገኝ አትችልም። ተስፋዬ በቀጥታ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር ብቻ ነው የሚነጋገረው። ዘመዱም ብትሆን ለሌሎች ጓዶች የሚያሳየውን ፍቅር ብቻ ነው የሚያሳይህ። በመሆኑም እኛ እንደቤተሰብ የምናውቀውን እንጂ የምንናገረው በኢሕአፓ ስለነበረው ሚና አብረውት ከሠሩት ሌላ የሚያውቅ አይኖርም። እኔ በማውቀው መሠረት ሰው አፍቃሪ፣ ትሁት፣ ልታይ ልታይ የማይል፣ ብዙ ከመናገር ብዙ ማድመጥ የሚወድ ሰው እንደነበር ልመሰክርለት እችላለሁ።” *አቶ በየነ ገብራይ ተስፉ*

## *አቶ ተወልደ ፍሡሕ ደበሳይ*

“በዚያ ጊዜ ልጅ ብሆንም ተስፋዬ ከቤተሰቦቹ ጋር ከጓደኞቹ ጋር ተቀምጦ የሚያደርገው ጭውውት ትዝ ይለኛል። ቤተሰባችንም ጋ ሲመጣ በታላቅ ደስታ እንቀበለው ነበር። እኔም ልጅ ብሆንም አንዳንድ ጊዜ ይዞኝ ይሄዳል። ቡና በወተት ይገዛልኛል። ስማቸውን ባልጠቅስም አሁንም በህይወት ያሉ አሲምባም አዲስ አበባም ከነበሩ ሰዎች ጋር ውይይት ያካሂዳል። ወደ ፒያሳ አራት ኪሎ ይዞኝ ይዞራል። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የኢሕአፓ እንቅስቃሴ ዕቡህ ሲገባ ቤተሰቦች የምናውቀው አሲምባ መሄዱን ነው። መጨረሻ ላይ ግብርና የእርሻ ሚኒስቴር ሠራተኛ የነበረው ንጉሴ አውዓላ ደሴ ውስጥ በውጫሌ ላይ ደርግ ጨፍጭፎ ከገደላቸው አንዱ ነበር። የሱን መሞት ሰምተን ሀዘን ላይ እያለን አዲስ አበባ ተከባ አሰሳ

ሲደረግ ተስፋዬ መሞቱ በሬድዮ ተነገረ ተሰማ። ጐረቤቶቻችን ጥቂት የሚያውቁት ነበሩ ግን አላጋለጡንም። የዚያ ጊዜ ዘመዱ መሆናችን ቢታወቅ ኖሮ እኛም ዛሬ ያለንበት ሕይወት አንደርስም ነበር። የቀሩትም አሁን አዲስ አበባ ያሉት አይኖሩም ነበር። እሱ መሞቱን ከሰማን በኋላ የነበሩ ሰነዶች ነበሩ አንድ ካርቶን ሙሉ ሰነድ አቃጥለን ቅጥያውንም ወደ ሽንትቤት ነው የጨመርን። ያንን አጠፋፋን የእኛ ቤት ሦስት ጊዜ ተፈተሸ። እዛው የነበረ ወንድሜ ፖለቲካ ውስጥ አይሳተፍም የመንግሥት ሠራተኛ ነበር ምንም ሌላ አደጋ አልደረሰብንም። ከዚያ በመቀጠል ወደ ሰባዎቹ አካባቢ ማጋለጥ ሲባል እኔ ያው ቀበሌ ውስጥ ወረቀት አንብቤሃለሁ ብዬ ተጋለጥሁ። ከዚያ ትምህርት ቤት የመኢሶን አባል የነበረ መምህር ጠቆመብኝ። ሆኖም አስቀድሜ ቀበሌ ያጋለጥኩበትን ወረቀት ይዤ ነበርና ምንም ሳልሆን ቀረሁ። ቀበሌ በሚደረግ የቀበሌ ወጣቶች ማህበር ውስጥ ተጠቁሜ ተመረጥሁና ቤተሰባችን ላይ የነበረውን በደርግ ሊመጣ የሚችለውን አደጋ ለመቋቋም ብንችልም ውስጤ ግን ተስፋዬና ቤተሰቦቼ ጋ ነው። አሲምባ፣ ኢሕአፓ በሙሉ ከህይወቴ ጋር በመሆኑ ውስጥ ውስጡን የኢሕአፓን ሥራ እየሰራሁና ኢሕአፓ የነበሩ ወገኖቼን እየተገናኘሁ ኖሬሃለሁ። ተስፋዬ  የሀገር ፍቅር የሕዝብ ፍቅር እንደነበረው ሌሎች እንደሚመሰክሩለት ሁሉ እኔም ይህን እላለሁ። አሲምባ ነበር ያልነው ወንድማችን አዲስ አበባ ተቀምጦ ሲታገልና ሲያታግል መውደቁን እንደማንኛውም ሰው በደርግ ሬድዮ ሰማን። ሕይወቱን ለተነሳበት ዓላማ አሳልፏል። ይህን ነው ማለት የምችለው። አመሰግናለሁ።" *አቶ ተወልደ ፍሡሕ ደበሳይ*

*'Wrong Move'*

*ዶር ተስፋዬ ደበሳይ አዲስ አበባ ከአንድ ጓደኛው ዶክተር ጋር ይኖር ነበር። ይህ ሰው በጊዜው ፖለቲካው ውስጥ ያልገባ ሙያዊ ሥራውን ብቻ የሚያከናውን ነው። ተስፋዬንም የፖለቲካ ተሳትፎ እንዳለው የሚያውቀው ጉዳይ የለም። ወሬአቸውም ሙያዊ ሥራቸው ላይ ያተኮረ ነው። ይህ በእንዲህ እያለ ለሁለቱም እውቅና ያለው ሰው አብሯቸው ይኖራል። በዚህ ሁኔታ ተስፋዬ ድርጅታዊ ሥራውን እያከናወነ በአለበት ወቅት አንድ ቄስ አጎቱ ከገጠር ይመጣሉ። ተስፋዬም እኚህን ቄስ ለዶክተር ጓደኛው ያስተዋውቃል። "ከገጠር ድረስ ሊጠይቀኝ የመጣ አጎቴ ነው" ብሎ ያስተዋውቃቸዋል። ቄሱም ከነነጭ ጥምጣማቸውና የለበሱትን ጋቢ እንዳጣፉ የሚተዋወቃቸውን ዶክተር እጃቸውን ደረት ኪሳቸው ሰደው መስቀል በማውጣት ካሳለሙ በኋላ ተዋውቀው የእንግድነታቸውን ይቀመጣሉ። ቄሱ ጠዋት ሲነሱ ዳዊታቸውን ደግመው፣ ማታ ሲተኙም ዳዊታቸውን ደግመው ነው። አማርኛቸውም የገጠር ነው። ምግብ ሲበሉም በጋራ ሲሆን ጸልየውና ቡራኬ ቆርሰው ለተስፋዬ፣ ለተስፋዬ ጓደኛ ዶክተር ለሌላው ሦስተኛ ሰውም ከሰጡና ማዕዱን ከባረኩ በኋላ ነው የሚበላው። እኚህ ቄስ እቤት ውስጥ ከዳዊታቸው በቀር ሌላ አያውቁም። ተስፋዬና ዶክተሩም የግል ጨዋታቸውን ሲያወጉ ቢገባቸውም ባይገባቸውም ዝም ብለው ያደምጣሉ። ተስፋዬና ዶክተሩ መዝናኛቸው ቼዝ ጨዋታ ነው። ለረዥም ጊዜ የሚፈጀውን ይህንን የቼዝ ጨዋታ ከተገናኙና ቤት ካሉ አዘውትረው ይጫወታሉ። ታዲያ አንድ ቀን እኚህ ቄስ አጠገባቸው ተቀምጠው ተስፋዬና ዶክተሩ ቼዝ ሲጫወቱ ዝም ብለው ይመለከታሉ። ጨዋታው እየፋመ…እየጋለ… ትኩረት እየሳበ ሁለቱ ተጋጣሚዎች እጅግ በተመሰጠ ሁኔታ ጨዋታቸውን አንዱ አንዱን*

ለመርታት ተያይዘውታል። ቄሱ ጨዋታውን እየተመለከቱ በመጡ ቁጥር ሳያስቡት እሳቸውም በጨዋታው ተመስጠዋል። የጨዋታው ዋናው መጠቃቃት ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ደርሷል። የዶክተር ተስፋዬ ኪንግ/King ቼዝ ኤንድ ቼክ ተብሎ ጨዋታው በዶክተሩ ጓደኛው አሸናፊነት ሊጠናቀቅ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ይገኛል። ሁለቱ ተጋጣሚዎች አጠገባቸው ቄሱ መኖራቸውን እንኳ ዘንግተዋል። ቄሱም ሀሳባቸው ከወትሮው በተለየ መልኩ ሁለቱ ሰዎች የሚያደርጉት የቼዝ ፍልሚያ ግራ ገብቷቸው ይሁን ሌላ ፈዘውና ተመስጠው ይመለከታሉ። ዶክተር ተስፋዬ ከመሸነፍ የሚያድነው የመጨረሻውን ወሳኝ እንቅስቃሴ ተረኛ ነው። ያለው ማምለጫ መንገድ አንድ እንቅስቃሴ ነው። ለበርካታ ደቂቃዎች አስቦ አውጥቶ፣ አውርዶ የመጨረሻውን ውሳኔ ሰጥቶ ሊያስኬድ የፈለገውን አንስቶ ሲያስቀምጥ ቄሱ ሳያስቡት "Wrong Move" አሉ። ተስፋዬም ዶክተሩም ዓይናቸው ፈጦ ያዩዋቸው ጀመር። ሦስቱም ፈዘውና ደርቀው ተፋጠው ቀሩ። ዶክተር ተስፋዬ ወዲያው "አልነገርኩህም ለካ በቅስናው ወደ ራሺያ በሄደበት ጊዜ ትንሽ ልምድ ስላለው ነው" ብሎ የሆነ ያልሆነውን በደነገጠ ሁኔታ ለዶክተሩ ለፈለፈ። ዶክተሩም ግራ ቢገባውም በዝምታ ተቀበለ።

ተስፋዬ ዶክተሩ ከሄደ በኋላ 'ምነው ምነው አዋረድከኝ ምነው' ብሎ ቄሱ ላይ አፈጠጠ። ቄሱም 'ምን ላድርግ አውቄ መሰለህ በጨዋታችሁ ተመስጬ ሳላስበው ነው' አሉ። እኚህ የገጠሬ አማርኛ ብቻ የሚችሉ ቄስ ዳዊት ደጋሚ ለኢሕአፓ ድርጅታዊ ሥራ አዲስ አበባ የመጡ ነብሱን ይማረውና ፀጋዬ ደብተራው ነበር።

ወደፊት ስለ ፀጋዬ ደብተራው ሥራዎች በሰፊው ለመዘገብ ቃል እየገባን የዛሬው የዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ 38ኛ ዓመት የሙት ቀን መታሰቢያ ጽሁፋችን መጋቢት 15 ቀን 2005 ዓ.ም. በአስነበብነው "ዝክረ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ" ላይ በወሰድነው ይቋጫል።

"ከድሀ ቤተሰብ ተወልዶ፤ ከመርፌ ቀዳዳ በጠበበች ዕድሉ ተጠቅሞ የዘመናዊ ትምህርት ዕድልን በማግኘት በፍልስፍና የዶክተሬት ማዕረግነት የተጎናጸፈው ዶር ተስፋዬ ዕውቀቱን ለሀገሩና ለድሃው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድገትና ብልጽግና የዘረጋውን ምኞቱንና ተስፋውን ሳያይ በጅምር ተቀጨ። "የተስፋዬ ዛፉ፤ ሲከረከም ቅርንጫፉ" እንዳለው ገጣሚ የተስፋዬ ተስፋ በተስፋ ቀረ። ብርሃን ዐይኑን ከደነ። በአጭር ተቀጨ። ተቀበረ።

ዶር ተስፋዬ ባለትዳርና የአንዲት ሴት ልጅ ሐምራዊት አባት ነበር። ሐምራዊት የአባቷን ጣዕም ሳታውቅ በሕጻንነታቸው ደርግ ወላጆቻቸውን ከበላባቸ፣ የአባት ወይም የእናት ወይም የሁለቱንም ጣዕም ሳያጣጥሙ፣ ሳያውቁ ካደጉት፣ የወላጆቻቸው አኩሪ ታሪክ እንኳ ያልተዳሰሰላቸው በርካታ የትላንት ሕፃናት የዛሬ ወጣቶችና ጎልማሳዎች ውስጥ ከሚመደቡት ናት።

«ያ ትውልድ ተቋም» ከተነሳበት ዓላማ አንዱ የዚያን ትውልድ ሰማዕታት መዘከርና ታሪካቸውን ለትውልድ ማስተላለፍ በመሆኑ የዶር ተስፋዬ ደበሳይን 38ኛ የሙት ዓመት መዘከር ስናስታውስ በጥልቅ ሐዘን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግልና ኢሕአፓ አንድ ሁነኛ መመኪያውንና መሪውን ያጣበት ቀን መጋቢት 15 ቀን 1969 ዓ.ም.። ኢትዮጵያ ሀገራችን አንድነቷን ጠብቃ የልጆቿ መብት የተከበረባትና ለሀገር ብልጽግናና ለልማት የተከፈለው የያ

ትውልድ ሰማዕታት ደም ከንቱ እንደማይቀርና ሁሌም በትውልድ ሲዘከር፡ ሲታወስ እንደሚኖርና የትግላቸውም ፍሬ ኢትዮጵያ ሀገራችንንና ልጆቿን ከፍ ከፍ እንደሚያደርጋት እምነታችን የጸና ነው።”

ለዚህ ሥራ ቀና ትብብር ላደረጉልን የዶክተር ተስፋዬ ልጁን ጨምሮ ቤተሰቦቹንና ጓደኞቹን እያመሰገንን ከመቃብር በላይ ስሙን በጀግንነት ተክሎ ያለፈው ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ለቤተሰቦቹ፣ ለኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች በመላ ሕዝብና ሀገር የሚኮራበት ጀግና መሆኑን በ «ያ ትውልድ ተቋም» ስም ልንገልጽ እንወዳለብን።

## *ምስጋና ከወ/ሮ ፍቅርተ ገ/ማርያም*

“ያ ትውልድ የሚያደርገው አስተዋጽዎ በዛሬው ቀን እንኳ ቀላል ነገር አይደለም። ካሰች ስለ ተስፋዬ አውርታ አታውቅም። ወይም አስቴር። ተስፋዬ ደበሳይ ሲደበቅ እንጂ ስለ ተስፋዬ ደበሳይ ሲወራ አይተው፣ ሰምተው አያውቁም። በዚህ በትግሉ አካባቢ ባሉ ሰዎች። ስለዚህ አሁን ስሰማቸው እነሱ እየተረባረቡ አንዴ ካሰች፣ አንዴ አስቴር፣ አንዴ ጽጌ ሲያወሩ አንጀቴን ነው የበሉኝ። ስለ ወንድማቸው ሲነገርላቸው፣ ተነግሮላቸው አያውቅም ነበር። ስለ ወንድማቸው ቤተሰብ ውስጥ ብቻ ባለ ነው፡ በትግሉ አካባቢ በነበረ ሰው ሰምተው አያውቁምና። በነሱ ስም ልናገር የምፈልገው ለዛ ትውልድ እግዚሃብሔር ይስጣችሁ ቋንቋም ችግር አለ። ለካሰችም፣ ለአስቴርም ዕድል ስለሰጣችሁ፣ ለእኛም ዕድል ስለሰጣችሁን እናመስግናለን። እነ ካሰች በትግል አካባቢ በነበሩ ሰዎች ስለ ተስፋዬ ሰምተው አያውቁም። ከእናንተ አሁን በመስማታቸው በጣም ደስ ይላቸዋል። ያ ትውልድ እግዝሃብሔር ይስጣችሁ ይሄን ስላደረጋችሁ። ከቤተሰቦቻቸው አካባቢ ብቻ ነው ስለ ተስፋዬ ደበሳይ የሚያወሩት፡ አሁን ግን አብረውት ከታገሉ እሱ ቆሞለት ለነበረው ትግል አብረውት ቆመው ካሉ ሰዎች ሲሰሙ ትልቅ ደስታ ነው፡ አመሰግናለሁ።” *ወ/ሮ ፍቅርተ ገብረማርያም።*

ዕድሜ ይስጠንና የዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ እና የሰማዕታት ወገኖቻችን ደም ተገቢውን ታሪካዊ ሥፍራ እንደሚያገኝ ጥርጥር አይኖረንም።

ቀጣይ ትውልድ ተስፋዬ ደበሳይንና መሰል ሰማዕታትን ሚዘክራቸው ቀን ዘላለማዊ ይሆናል!

«ያ ትውልድ ተቋም»

መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዋቢ ጽሁፎችና መረጃዎች

- «ያ ትውልድ ተቋም» ፓል ቶክ ውይይት፡ ሜይ ዴይ 2005 ዓ.ም. http://yatewlid.com/audio%20page.htm
- “ዝክረ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ” ፡«ያ ትውልድ ተቋም» መጋቢት 15 ቀን 2005 ዓ.ም. http://yatewlid.com/index_htm_files/032413_Dr_Tesfay_Debesay.pdf
- “ፍጹም ነው እምነቴ” የከፍተኛ 15 ቀይ ሽብር እውነተኛ ታሪክ፡ ነሲቡ ስብሐት፡ መስከረም 2007 ዓ.ም. http://yatewlid.com/index_htm_files/YTT_FNE_Announcement_Marketing.pdf

www.yatewlid.com, www.yatewlid.org

yatewlid@yahoo.com
yatewlid@gmail.com
yatewlid@hotmail.com